
# የእውነታ ሉህ ቁ. ፯
# የዘር ልዩነት ድህነት በሥራ መቀጠር ላይ ያለው ተጽእኖ

## በዘረኝነት የተለዩ ሰዎች በሥራ ስምሪት ውስጥ ጉዳታቸው እንዴት ነው?

በዘረኝነት ተጽዕኖ ምክንያት ጉልህ የሆነ የደሞዝ መጠንና የሥራ ቅጥር ክፍተቶች በካናዳ ውስጥ አሉ። ክፍተቱንም ጠለቅ ያለ እና ሰፋ የሚያደርጉት ምክንያቶች-በሥራ ቀጠራ እና በዕድገት ጭማሬ ላይ ያለ ስልታዊ ዘረኝነት ነው።
የዓለም አቀፍ ማስረጃዎችን እና ልምድን ባለማወቃቸው ምክንያት የስደተኞችን ሞያዊ ክህሎት እውቅናን ሰጥቶ ያለመቀበል፣ እንዲሁም አመልካቾች ላይ አድልዎ ለማድረግ የፖሊስ ዘገባን መጠቀም ።



**በዘር መለየት ምክንያት ያለ የሥራ አጥነት ሁኔታ፡** በኦንታሪዮ ውስጥ የሚኖሩት ቀለም ያላቸው ሰዎች ከነጭ ነዋሪዎች ይልቅ የሥራ አጥነታቸው መጠን ከፍ ያለ ነው።

በዘር የተለዩ ወንዶች የዘር ልዩነት ከሌላቸው ከሌሎች ወንዶች ይልቅ የሥራ አጥነት ዕድላቸው 24% ያህል ከፍ ያለ ነው ።
በዘር የተለዩ ሴቶች የዘር ልዩነት ከሌላቸው ወንዶች ይልቅ የሥራ አጥነት ዕድላቸው በ43% ያህል ከፍ ያለ ነው ።

**ስደተኛ ሠራተኞች፡-** ከ 2000 ወዲህ በካናዳ የጊዜያዊ ስደተኛ ሠራተኞች ቁጥር በአራት እጥፍ አድጓል።
እ.ኤ.አ. እስከ 2018 ድረስ በአገሪቱ ውስጥ 429,340 ያህል ጊዜያዊ ሠራተኞች ነበሩ።
ከዓለማችን ደቡባዊ ክፍል አካባቢ ለጊዜያዊነት ሥራ የሚመጡ ሠራተኞች ፍሰት - ከደቡብ የዓለም ክፍል የሚመጡ ያልተመጣጠኑ የቀለም ሠራተኞች በተለየ መልኩ ለብዝበዛ እና ለጥቃት የተጋለጡ ናቸው።

**ዘረኝነት፡-** በኦንታሪዮ ውስጥ ያሉ ስደተኛ የእርሻ ሠራተኞች አብዛኛዎቹ ከሜክሲኮ እና ከካሪቢያን የሚመጡ ሲሆን የሚሰጣቸው የህግ ጥበቃ ሽፋን በጣም ትንሽ ነው።
አንድ ጥናት እንዳመለከተው 75% የሚሆኑት ስደተኛ የእርሻ ሰራተኞች ከአሜሪካ ይልቅ በካናዳ ውስጥ የበለጠ ዘረኝነት እንደሚያጋጥማቸው ነው።

**አደገኛ ሥራ፡-** የዘር ልዩነት ያላቸው ሰዎች - የአገሬው ተወላጅ ሕዝቦች፣ የቀለም ሕዝቦች - እና ስደተኞች በዝቅተኛ ደሞዝ ፣ ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅሞች አለመኖርና የሥራ ዋስትና ያለመኖር የመሳሰሉት እንከኖች ባሉባቸው የከፊል-ሰዓት ሥራ፣ በአደገኛ ሥራ መስኮች በብዛት የሚሠማሩ ናቸው።

በቀለም ሠራተኞችና በስደተኛ ሰራተኞች ላይ የሚደረጉ መጠን-የለሽ ተፅእኖ ጉዳዮችን ለመፍታት የተዘጋጀ የመንግስት ዕቅድ የለም።
አሠሪዎች የቅጥር ደንቦች አቅርቦቶችን ያለ ቅጣት ይጥሳሉ፤ በቀጣሪዎች ልግምትና እንቢተኝነት ምክንያትም ተቀጣሪዎች ያልተከፈላቸውን ደመወዝ መመለስ አለመቻል፤

እንዲሁም አንድ ሰው ስራውን እንዳያጣ እና በማህበረሰቡም ውስጥ ስሙ እንዳይጠፋ መፍራት - እንደዚህ ያለ ፍርሃትም በአገሬው ተወላጅ ማህበረሰቦችና እና በቀለም ማህበረሰቦች ዘንድ እጅግ ከፍ ያለ ነው።

## የነባር የአገሬው ተወላጅ ትኩረት

እ.ኤ.አ. በ 2015 ነባር የአገሬው ተወላጅ ሰዎች በአብዛኛዎቹ “እውቀት የሚጠይቁ ሥራዎች” ውስጥ ዝቅተኛ ተሳትፎ ነበራቸው - ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በላይ እውቀት የሚጠይቁ እና የተሻለ ደመወዝ የሚያስገኙ ሙያዊ ፣ የአስተዳደርና ቴክኒካዊ ሥራዎች ናቸው። እነዚህም የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑ ሰዎች ይልቅ በአስተዳደራዊ ስራዎች (7.1% ከ 9.5%) ወይም ከንግድ፣ ፋይናንስ እና አስተዳደራዊ የሥራ መስኮች (ከ 14.4% እና ከ 17.0%) ጋር የመሥራት ዕድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡
እ.ኤ.አ. በ 2018 በቀረበው የጤና ሪፖርት መሠረት ነባር የአገሬው ተወላጅ ህዝቦች ከኦንታሪዮ አማካይ 7% ጋር ሲነፃፀር 63% ያህል ሥራ አጥ የነበሩ ሲሆን 87% ያህል ደግሞ ከ LICO መስፈርት በታች ይኖራሉ።
ሙሉ ሰዓት የሚሠሩት ነባር የአገሬው ተወላጅ ሠራተኞች በ2015 በአማካይ በሰዓት 26 ዶላር ያገኙ ሲሆን የአገሬው ተወላጅ ያልሆኑት አጋሮቻቸው ግን በአማካይ በሰዓት 27.41 ዶላር እንዲያገኙ ይደረጋል።

“ - ሥራዬን አጣሁ ፣ ተርቤአለሁ፡፡ ለልጆቼ ገንዘብ እፈልጋለሁ... በሚገባም ማሰብ አልችልም... የሰጡኝ ‹የይገባኛል› ቅጽ ፣ በጣም የተወሳሰበ ነው ... ምርመራው እስኪያልቅ ድረስ ስምንት ወራት ፈጅቷል፡፡

- ሀሰን በ 7000 ዶላር ባልተከፈለ ደሞዝ ስለቀረበ የይገባኛል ጥያቄ ”




እ.ኤ.አ. ከ 1987 እስከ 1992 ባሉት 5 ዓመታት ውስጥ፣ ዝቅተኛ ገቢ ከሚያገኙ 72% (10 ከመቶ በታች) የገቢ መሰላላቸው ወደ ላይ ከፍ ብሎ ነበር፤ ሆኖም ከ 2007 - 2012 ባለው ጊዜ ውስጥ ግን ይህ መቶኛ ወደ 60% አሽቆልቁሎአል፡፡

## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው፡፡ እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው፡፡
ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው፡፡
በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑት በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች ናቸው፡፡
በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚሆኑት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው፡፡

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው፡፡

ስልታዊ ዘረኝነት ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው፡፡
የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡

**የትምሕርትና የሥራ መረጃ ጽሑፎች፡** - ስደተኞች የሚያቅርቧቸው የትምሕርትና የሥራ ልምምድ ማስረጃዎች ሁልጊዜ ዝቅተኛ ግምት ይሰጣቸዋል ወይም ዋጋቢስ ሆነው እንዲቆጠሩ  ይደረጋል፡፡ በመሆኑም በከባድ ድህነት (በLICO ስር ለተከታታይ 5 ዓመታት) ከሚኖሩ ስደተኞች ውስጥ 41% የሚሆኑት ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡

**የስም ጦስ፡** በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አመልካቾች ተመጣጣኝ የሆነ የትምህርት እና የስራ ልምድ ቢኖራቸውም እንኳ ስማቸው (ያጠራር ድምጽ) ከአፍሪካ፣ ከእስያ ወይም ከሙስሊም ጋር የሚመሳሰል ከሆነ አሠሪዎች በአመልካቾች ላይ ከባድ አድልዎ እንደሚያደርጉ ያሳያል፡፡ ድሆች ቢሆኑም (ለ5 ዓመታት ያህል ከኤል አይ ሲ ኦ LICO በታች የቆዩ) ስደተኞቹ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡

**የፖሊስ ጥበቃ፡** በሠራተኞች መቅጠር ሂደት አሠሪዎች የፖሊስ ምርመራ ስለሚጠቀሙ የፖሊስ ክትትሉ ደግሞ ከመጠን በላይ ሲሆን ለነባር የአገሬው ተወላጆች፣ ለጥቁሮችና እና ለሌሎች የቀለም ማህበረሰቦች ከስራ ገበያው ውጭ የማገድ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

**አድልዎ**: በርካታ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በሠራተኛው ኃይል ውስጥ አድልዎ ፣ ከፍተኛ የሥራ አጥነት መጠን ፣ ደህንነት ያለመጠበቅ ብዛት/ አደገኛ የሥራ ሁኔታ፣ ዝቅተኛ የደሞዝ ክፍያ እና አናሳ ገቢ በዘር መለየት አድልዎ ሥር የሚኖሩ ቤተሰቦች በድህነት አዘቅት ውስጥ እንዲኖሩ የማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡



**በሥራ ላይ ተሠማርተው እያሉ ጉዳት የሚደርስባቸው ሠደተኞች በግዴታ ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲመለሱ ይደረጋል፤ ይህም ሠራተኞቹ አስፈላጊውን ህክምና እንዳያገኙ ይከለክላቸዋል፣ የሚያስፈልጋቸው ህክምናው ራሱ በገዛ አገራቸው ውስጥ የማይገኝ ሊሆን ይችላል፣ በተጨማሪም ሰራተኞቹ ሊያገኙት የሚገባ ጥቅም ወይም ካሳ በሚገባ እንዳያገኙ ይከለክላቸዋል ማለት ነው፡፡**

# ምን እየተደረገ ነው?

ቶሮንቶ ኮሚኒቲ በነፊትስ ኔትዎርክ (TCBN) በትልቋ ቶሮንቶና አካባቢዋ ውስጥ የሥራ ቅጥር፣ የሥራ ልምድን የመማር ዕድሎች፣ እኩልነት ለሚፈልጉ ቡድኖች፣ እንዲሁም ታሪካዊ ጉዳት ላለባቸው ማኅበረሰቦች በሁሉም የሕዝብ መሠረተ ልማት ተቋማት ፕሮጀችቶች ውስጥ የሥራ ስምሪት እና የሥራ ሥልጠና ዕድሎችን ለማስጠበቅ ይሠራል፡፡
www.communitybenefits.ca / info@communitybenefits.ca

የኦንታሪዮ የነባር የአገሬው ተወላጅ የወዳጅነት ፌዴሬሽን ማዕከላት
ነባር የአገሬው ተወላጅ ማህበረሰብ በስራ እና በትምህርት ዓላማዎች ፣ በቤተሰብ ፣ በጤና ፣ በፍትህ እና በሌሎች ብዙ አገልግሎቶች ውስጥ ድጋፍ ለማፈላለግ የባህላዊ ማዕከሎች መረብ ነው፡፡
www.ofifc.org / ofifc@ofifc.org